የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

AFAR REGION NEGARIT GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

1ኛ ዓመትቁጥር 4 ሠመራ የካቲት 9 ቀን 1990 ዓ.ም	በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ	1st Year No. 4 Samara 16th, 1998

ማውጫ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ..... ገጽ 1

አዋጅ ቁጥር 4/1990 ዓ.ም

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ ሕገ መንግስት ነፃ የዳኝነት አካል የተቋቋመ በመሆኑ፣

ይህንኑ በሕገ መንግስት የተረጋገጠውን የዳኝነት ነፃነት ለማረጋገጥ ከሚያስችሉት መሠረታዊ ጉዳዮች አንዱና ዋነኛው የዳኞች አስተዳደርን ከማናቸውም የመንግስት አካል ወይም ባለስልጣን ተፅዕኖ ነፃ በሆነ ሁኔታ እንዲመራ ማድረግ በመሆኑ፣

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47(2-2) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 4/1990» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

1. «የዲሲፕሊን ጥፋት» ማለት በዲሲፕሊንና በሥነ ምግባር ደንብ የተመለከተው ጥፋት ሲሆን በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛነቱ የተረጋገጠበትን በጉቦና በአማላጅ የሚሠራን በዘር በሃይማኖት በፆታ በፖለቲካ አመለካከት አድሎዎ የሚየደርግና ወይም ባለጉዳይ የሚያጉላላን ይጨምራል።
2. «ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና ማነስ» ማለት በዲሲፕሊንና በሥነምግባር ደንብ የተመለከተው ሲሆን በዳኝነት ሥራው ላይ ሙያው ከሚጠይቀው የትምህርትና የልምድ ችሎታ በታች የሆነ የሕግና የፍሬ ነገር ስህተት የሚፈጽምን ወይም ከሚገባው ጊዜ በላይ ክርክር የሚያራዝምን ይጨምራል።
3. «ዳኛ» ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተሾመ ዳኛ ነው።
4. «ምክር ቤት» ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ምክር ቤት ነው።
5. «ሰው» ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

3. <u>የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ መቋቋም</u>

የክልል መንግስት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ /ከዚህ በኋላ «ጉባኤ» እየተባለ የሚጠራ/ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

4. <u>የጉባኤ አባላት</u>

1. በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 65(1) መሠረት ጉባኤው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል።

ሀ/ የጠቅላይ ፍ/ቤት ኘሬዝዳንት

ለ/ የጠቅላይ ፍ/ቤት አንድ ዳኛ

ሐ/ ከዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ሁለት ዳኞች

መ/ ከጠበቆች ማህበር አንድ ተወካይ

ሠ/ ከክልሉ ምክር ቤት ሶስት ተወካዮች

ረ/ ከተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች ሶስት ሰዎች

ሰ/ የክልሉ ፍትህና አቃቢ ህግ ቢሮ ኃላፊ

ሸ/ የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽነር

ቀ/ በክልሉ ከሚገኙ ወረዳዎች ሶስት ዳኞች

2. በዚሁ ጉባኤ አባላት ስለሚሆኑት ዳኞች አመራረጥ የዳኝነት ሹመት ቀደምትነትን መሠረት በማድረግ ይሆኛል።

5. <u>የጉባኤው አመራር</u>

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዝዳንት የጉባኤው ሰብሳቢ ይሆናል ሆኖም ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ም/ኘሬዝዳንት የሰብሳቢውን ሥራ ተክቶ ይሠራል።
2. ጉባኤው የራሱን ፀሐፊ ከአባላቱ መካከል ይመርጣል።

6. የጉባኤው ስልጣንና ተግባር

ጉባኤው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል።

1. በጉባኤው አባላት ከተጠቆሙ እጩዎች መካከል በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 9 መሠረት ለዳኝነት ብቁ የሆኑትን እጩ ዳኞች ይመርጣል።
2. የክልሉ ዳኞች ሬጂስትራሮችና ተከላካይ ጠበቆች የሚመሩበትን የሥነ ምግባርና የዲሲፕሊን ደንብ ያወጣል።
3. የክልሉን ዳኞች ምደባ ዝውውር አበልና ደመወዝ ይወስናል።
4. በዳኞች ላይ የዲሲፕሊን ቅጣት የመወሰን እንደአግባቡ ሁኔታ ከዳኝነት ሥራ የማገድ እንዲነሳ የመወሰን።

5. ሬጅስትራሮችንና ተከላካይ ጠበቆችን መርጦ ይሾማል እድገታቸውን ዝውውራቸውን ደመወዛቸውንና የአገልግሎት ዘመናቸውን ይወስናል የዲሲፕሊን እርምጃ ይወስዳል ከሥራ ያሰናብታል።
6. ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም ሲባል እንደአስፈላጊነታቸው በየዘሉ ፍርድ ቤቶች ንዑስ ጉባኤዎችን ያቋቁማል ስልጣንና ተግባራቸውንም ይወስናል።
7. የዳኝነት ሥራን ለማቀላጠፍ የሚረዱ ጥናቶች እንዲካሔዱ ያደርጋል።

7. <u>የጉባኤው ስብሰባ</u>

1. ጉባኤው በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወይም ከጉባኤው አባላት መካከል (2/3) ሁለት ሶስተኛው ሲጠይቅ ጉባኤው ስብሰባ ለማድረግ ይችላል።
2. ከጉባኤው አባላት መካከል ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል።
3. የጉባኤው ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ። ሆኖም ድምጽ እኩል በኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።
4. የዲስኘሊን ክስ የቀረበበት ማንኛውም የጉባኤው አባል ዳኛ ጉዳዩ በሚታይበት ጊዜ በጉባኤው ስብሰባ ላይ በአባልነት መቀመጥ አይችልም።
5. ጉባኤው የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ማውጣት ይችላል።

8. <u>የጉባኤው ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር</u>

የጉባኤው ሰብሳቢ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

1. የጉባኤውን ጸሐፊት ቤት በበላይነት ይመራል ይቆጣጠራል።
2. የጉባኤውን ስብሰባ ይጠራል።
3. የጉባኤውን ስብሰባ በሊቀ መንበርነት ይመራል።
4. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በጉባኤ አባላት የተጠቆሙትን ግለሰቦች አጭር የሕይወት ታሪክ መግለጫ አዘጋጅቶ ለጉባኤው ያቀርባል በጉባኤው የተመረጡትን እጩ ዳኞች ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር በማቅረብ በም/ቤቱ እንዲሾሙ ያደርጋል።

9. <u>ለዳኝነት ለመመረጥ የሚያበቁ ሁኔታዎች</u>

የሚከተሉት ሁኔታዎች የሚያሟላ ማንኛውም ሰው ዳኛ ሆኖ ሊሾም ይችላል።

1. በሕግ ትምህርት የሰለጠነ ወይም በልምድ የሕግ እውቀት ያካበተ።
2. በታታሪነቱ በፍትሐዊነቱና በሥነ ምግባሩ መልካም ስም ያተረፈ።
3. የአእምሮ በሽታ የሌለበት።
4. ኢትዩጵያዊ የሆነና ቢቻል የክልሉን ቋንቋ የሚያውቅ።
5. በዳኝነት ሙያ ለመሠማራት ፈቃደኛ የሆነ።
6. እድሜው ከ 21 ዓመት ያላነሰ።

10. <u>ስለዳኞች አሿሿም</u>

የክልሉ ዳኞች አሿሿም በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 64 መሠረት ይፈፀማል።

11. <u>ቃለ መሀላ</u>

ዳኞች ሥራቸውን ከመጀመራቸው በፊት የሚከተለውን ቃለ መሀላ ይፈጽማሉ።

እኔ ---------- በዛሬው እለት የ ---------- ፍርድ ቤት ዳኛ በመሆን ተሹሜ ሥራዬን ስጀምር የተጣለብኝን ከፍተኛ ኃላፊነት በታማኝነት ለመፈፀም ቃል እገባለሁ።

12. <u>የዳኝነት ነፃነት</u>

1. ዳኞች የዳኝነት ሥራቸውን በነፃነት ያከናውናሉ ከሕግ በስተቀር በሌላ አይመሩም።
2. በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 13 እና 14 በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ዳኞች ከሥራቸው አይነሱም።
3. ማንኛውም ዳኛ ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ሳይፈቅድ አይያዝም አይታሰርም።

13. <u>ዳኞች ከሥራ ስለሚነሱበት ሁኔታ</u>

1. ማንኛውም ዳኛ ከሥራ የሚሠናበተው በሚከተሉት ምክንያቶች ይሆናል።

   ሀ/ ሥራውን ለመልቀቅ ሲፈለግ የሁለት ወር የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ለዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በማቅረብ።

   ለ/ እድሜው ስድሳ (60) ዓመት ሲሞላው በጡረታ።

   ሐ/ በሕመም ምክንያት ዳኛው ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን አይችልም ተብሎ በጉባኤው ሲወሰን።

   መ/ በዲሲፕሊን ጥፋት ፈጽሞ ሲገኝ።

   ሠ/ ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና የሌለው መሆኑ በጉባኤ ሲወሰን።
2. የማንኛውም ዳኛ የጡረታ መውጫ እድሜ አይራዘምም።

14. <u>አቤቱታ ስለማቅረብ</u>

1. ማንኛውም ሰው በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 13 የተመለከቱትን ተላልፎ በሚገኝ ዳኛ ላይ ለጉባኤው አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።
2. ጉባኤው የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል ሆኖም የጉባኤው ውሳኔ ተግባራዊ የሚሆነው ውሳኔው ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በምክር ቤቱ አባላት በአብላጫ ድምጽ ሲፀድቅ ይሆናል።

15. <u>የተሻሩ ሕጎች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ መመሪያ ወይም ውሳኔ በዚህ አዋጅ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

16. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከየካቲት 9 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሠመራ የካቲት **9** ቀን **1990** ዓ.ም

እስማኤል አሊ ሲሮ

የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት

ርዕሰ መስተዳድር